በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**መጋቢት ፲፩ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

- ‹‹እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፡፡›› ***<u>ሮሜ 12፡3</u>*** ተብሎ እንደተጻፈው አንዱ ሰው ከሌላው የሚለየው በእምነት ደረጃውና በእምነቱ ዓይነት ነው፡፡
- አንዳንድ ሰዎች ጥቂት እምነት ያለው ሰው በጭራሽ አማኒ እንዳልሆነ አድርገው አጋነው ለመናገር ሲሞክሩ ይደመጣሉ፡፡ ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚጋጭ ፍርደ ገምድልነት ነው፡፡
- አንዳንዶችም ‹‹አማኝ›› የሚለውን ቃል ‹‹የተመረጡ›› ከሚለው ቃል ጋር አጋጭተው አንድ አስመስለው ያቀርባሉ፡፡
- ለማንኛውም አስቀድመን የተለያዩ የእምነት ደረጃዎችን አስመልክቶ ትምህርተ ቤተ ክርስቲያናችንን እንመልከት፡፡

1. ***አዲስ አማኝ የሆነ ክርስቲያን እምነት አለ፡፡*** ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ያለውን አማኝ ‹‹ትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፡፡›› ***<u>ቀዳ ጢሞ 3፡6፡፡</u>*** ለመንፈሳዊ አገልግሎት መሾም እንደማይገባው የማይሸከመውንም ክብር እንዳይሰጡት አስጠንቅቋል፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

2. ***ጥቂት ወይም ያልበረታ እምነት ያላቸው አሉ፡፡ ስለእነዚህም በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተጻፈው የሚያስረዳን አለ፡፡***

   i. ስለ ምግብና ስለ ልብስ እግዚአብሔርን የሚያማርሩ ናቸው፡፡ ጌታችንም ለእነዚህ የምድር አበቦችን እንደ ምሳሌ አቅርቦ ጠቢቡ ሰሎሞን አንኳ ከክብሩ ከአበቦቹ እንደ አንዱ እንዳልለበሰ በመግለጽ ‹‹ ስለ ልብስስ ስለ ምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፤ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም። እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት? ›› ***<u>ማቴ 6፡28-30 ፤ሉቃ 12፡28፡፡</u>*** በማለት ገስጾአቸዋል፡፡

   ii. ጌታችን በባሕር ላይ መራመድ ከጀመረ በኋላ መስመጥ ሲጀምር በመጠራጠሩ ‹‹ ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና። አንተ እምነት የጎደለህ፥ ስለምን ተጠራጠርህ? ›› ***<u>ማቴ 14፡31፡፡</u>*** በማለት የገሰጸውን ጴጥሮስን የሚመስሉ ናቸው፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

2. ***ጥቂት ወይም ያልበረታ እምነት ያላቸው አሉ፡፡ ስለእነዚህም በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተጻፈው የሚያስረዳን አለ፡፡***

   iii. **ጌታችን በእንቅልፍ ሆኖ ማዕበሉ የሚጓዙበትን ታንኳ ሲያነዋውጥ አይተው የፈሩትን ደቀ መዛሙርቱም** ‹‹እርሱም፡- እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ?›› ***<u>ማቴ 8፡26፡፡</u>*** **ብሎአቸዋል፡፡**

   iv. **ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ** እንጀራ ባንይዝ ነው ብለው እርስ በርሳቸው **ሲነጋገሩ** ‹‹ለአምስቱ ሺህ አምስቱ እንጀራ፥ ስንት መሶብም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን? ወይስ ለአራቱ ሺህ ሰባቱ እንጀራ፥ ስንት ቅርጫትም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን? ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ እንድትጠበቁ ብዬ ስለ እንጀራ እንዳልተናገርኋችሁ እንዴት አታስተውሉምን? ›› ***<u>ማቴ 16፡7-11፡፡</u>*** **ብሎ ገስጾአቸዋል፡፡**

   - **በእግዚአብሔር ረዳትነት መጠራጠርና ከርሱም የሚመነጭ ፍርሐት የእምነት ማነስ ምልክት ነው፡፡**

   v. **ሐዋርያት ቅዱስ ጳውሎስ ከእምነቱ ማነስ የተነሳ አትክልት ብቻ የሚበላውን ሰው አስመልክቶ ማንም ሰው እንዳይፈርድበትና እንዳይንቀውም…**

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

2. ***ጥቂት ወይም ያልበረታ እምነት ያላቸው አሉ፡፡ ስለእነዚህም በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተጻፈው የሚያስረዳን አለ፡፡***

   v. ‹‹በእምነት የደከመውንም ተቀበሉት፥ በአሳቡም ላይ አትፍረዱ። ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደ ተፈቀደለት የሚያምን አለ፥ ደካማው ግን አትክልት ይበላል። የሚበላ የማይበላውን አይናቀው የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ፥ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና። አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል።›› ***<u>ሮሜ 14፡1-4፡፡</u>*** **በማለት ጽፎልናል፡፡**

- **በዚህ መካከል ጌታችን ልጁ በክፉ መንፈስ የተያዘበትን ጌታችንም ‹‹ታምናለህን?›› ሲለው** ‹‹ አምናለሁ፤ አለማመኔን እርዳው አለ። ›› ***<u>ማቴ 9፡24፡፡</u>*** **ያለውን አባት እናደንቀዋልን፡፡**
- **በእምነቱ ደካማ የሆነ ሰው እግዚአብሔር ይረዳው ዘንድ ስለ እርሱ የሚጸልዩለት ቅዱሳን ያስፈልጉታል፡፡ እንዲህ ያለውንም ሰው እግዚአብሔር ይረዳዋልና ልንንቀው አይገባም፡፡**

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፬

## የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው

## የእምነት ደረጃዎች

### *3. የተወሰነ እምነት ያላቸው ሰዎች*

- እንዲህ ያሉ ሰዎች በእግዚአብሔር የሚያምኑት በተወሰነ መጠን ሲሆን እምነታቸውም ከዚያ መጠን አያልፍም፡፡ እንዲህ ላለው እምነት ምሳሌ የምናደርጋቸው ወንድማቸው እንዳይሞት ከሕመሙ ሊያድነው እንደሚችል በጌታችን ያመኑት ማርያምና ማርታ ናቸው፡፡ ቢሞትም እንኳ ወዲያው ሊነሳ እንደሚችል የሚቀበሉበት እምነት ግን አልነበራቸውም፡፡
- ስለዚህ ማርታና ማርያም እያንዳንዳቸው ለጌታችን ‹‹ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር፡፡›› ብለውታል፡፡ ***ዮሐ 11፡21፣ 32፡፡*** ጌታችንም ማርታን ‹‹ወንድምሽ ይነሣል›› ሲላት ‹‹በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው።›› ***ዮሐ 11፡24፡፡*** ጌታችንም ወደ መቃብሩ ሄዶ ‹‹ድንግዩን አንሡ›› ሲላቸው ማርታ ‹‹ጌታ ሆይ፥ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል አለችው።›› ***ዮሐ 11፡39፡፡***
- ጌታችንም ይህን የተገደበ እምነት እንዲያድግ ዕድል ሰጠ እንጂ ቸል አላለም ፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪

## የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው

## የእምነት ደረጃዎች

### *3. የተወሰነ እምነት ያላቸው ሰዎች*

- ስለዚህም ነው ማርታን ‹‹ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል… ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታዪ አልነገርሁሽምን? ›› ያላት፡፡ ***ዮሐ 11፡25፣ 40፡፡***
- ጌታችን አልአዛርን ከሞት በማንሣት የእግዚአብሔርን ክብር እንድታይና እንድታምን ተአምራቱንም ያዩ አይሁድም ያምኑ ዘንድ አደረጋቸው፡፡
- በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው ተአምር ከእምነት በኋላ እንጂ በፊት አልነበረም፡፡
- ይህም ከሞተ አራት ቀን ሆኖት የሚሸት ሬሳ ሲነሳ የመጀመሪያው ተአምር ሆኖ የተደረገ አይደለምን?

### *4. ዝግ ያለ ልብ እምነት*

- ይህም ለማወቅ ወይም ለመረዳት ዝግተኛ ከመሆን የሚመጣ ይሆንና እንዲህ ያለውም ሰው እምነት በፍጥነት የማይገለጥ ይሆናል፡፡
- ይህም ዓይነት እምነት የኤማሁስ መንገደኞች ስለ ጌታችን ትንሣኤ የነበራቸውን እምነት የሚመስል ነው፡፡ እነዚህን የኤማሁስ መንገደኞችም ጌታችን …

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፱</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

### *4. ዝግ ያለ ልብ እምነት*

- ‹‹እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? ›› ***<u>ሉቃ 24 25-26፡፡</u>*** **በማለት ገስጾአቸዋል፡፡**
- **በመቀጠልም ስለርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጎመላቸው፤ ከነበራቸው ጥቂት መረዳት ወይም ዕውቀት የተነሳ የነበረውን መዘግየት ፈውሶ ለማመን አበቃቸው፡፡ ይህም የሚነግረን ስለ እምነት የሚኖረውን ጥርጥር ሁሉ ማጥራት እንደሚገባ ነው፡፡**
- **ምንም መልካም ውጤት የማያመጣውን እውነተኛውንም እምነት ለመገንዘብ የማያስችለውን መንገድ ተከትሎ ሰውን ከማቃለልና ከመግፋትም ከላይ የተመለከትነው የመመለስና የሚያስተምር የሆነ ይህ መንገድ የተሻለ ነው፡፡**

### *5. አደገኛ የሆነ እምነትም አለ፤ እርሱም የሞተ እምነት ነው*

- **ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ** ‹‹እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።›› ***<u>ያዕ 2፡17፣20፡</u>*** **እንዲህ ያለ እምነት ሰውን እንደማያድነው** ‹‹እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?›› ***<u>በማለት ያዕ 2፡14</u>*** **በመጠየቅ የሚያድን…**

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

### *5. አደገኛ የሆነ እመነት አለ እርሱም የሞተ እምነት ነው*

- … እምነት ሥራና ፍሬ እንደሚያስፈልገው ‹‹እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ፡፡›› ***<u>ያዕ 2፡18</u>*** በማለት ነግሮናል፡፡

### *6. ጽኑእ ያልሆነ እምነትም አለ*

- እንዲህ ያለው እምነትም ጌታችን ከመያዙ አስቀድሞ ለጴጥሮስ የተናገረው ዓይነት ነው፡፡ ‹‹ጌታም፡- ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ።›› ***<u>ሉቃ 22፡31-32፡፡</u>*** በዚህ ወቅት የጴጥሮስ እምነት ጽንዓት የጎደለው የነበረ ቢሆንም በኋላ ግን ወደ ቀደመው ጽኑእ እምነቱና ብርታቱ ተመልሷል፡፡

### *7. ሌላው መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ከእውነተኛ እምነት(ሃይማኖት) ስለ ወጣው እምነት ነው*

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ያለውን እምነት ሲገልጽ ‹‹ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።›› ***<u>ቀዳ ጢሞ 5፡8፡፡</u>*** ብሏል፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

7. ***ሌላው መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ከእውነተኛ እምነት(ሃይማኖት) ስለወጣው እምነት ነው***
2. ***ሥጋዊ ስሜታቸው ለክርስቶስ ያለውን መገዛታቸውን ስላጠፋባቸው ብልቴቶችም*** ‹‹ባል የሞተባቸውን ቆነጃጅት ግን አትቀበል፤ በክርስቶስ ላይ ተነሥተው ሲቀማጠሉ ሊያገቡ ይወዳሉና፤ የፊተኛውንም እምነታቸውን ስለ ናቁ ይፈረድባቸዋል›› ***<u>ቀዳ ጢሞ 5፡11-12፡፡</u>*** **ብሏል፡፡**
3. **በተጨማሪም** ‹‹ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ። ›› ***<u>ቀዳ ጢሞ 6፡10፡፡</u>*** **ብሏል፡፡**
4. ***<u>በቀዳ ጢሞ 6፡20-21፡፡</u>*** ‹‹ጢሞቴዎስ ሆይ፥ በውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ፥ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ፤ ይህ እውቀት አለን ብለው፥ አንዳንዶች ስለ እምነት ስተዋልና። ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን።›› **ብሏል፡፡**

- **በእነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች የእምነትንና የሥራን ትስስር እንክዳለንን? በማይገባ ሥራ ሰው እምነቱን እንደካደ (ከእምነቱ ፈቀቅ) እንዳለ፣ ተሳስቶ እንደወደቀ ተነግሮናልና፡፡**
- **እነዚህን ምሳሌዎች እንደ መመዘኛ በመውሰድ ሐዋርያው** ‹‹በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ›› ***<u>ካል ቆሮ 13፡5</u>*** **እንዳለን ራሳችችንን ልንመረምር ያስፈልገናል፡፡**

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪

## የእምነት ደረጃዎች

### *8. ከሁሉ የከፋው ደግሞ እምነትን (ሃይማኖትን) መካድ ነው*

- **ሐዋርያው** ‹‹ መንፈስ ግን በግልጥ። በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል ፡፡›› ***ቀዳ ጢሞ 4:1፡፡***
- **ሃይማኖትን መካድ በሃይማኖት ቆይቶ ሃይማኖቱን መተው ማለት ነው፡፡**
- **ሐዋርያው ከጌታችን ዳግመኛ መምጣት (ከምጽአት) አስቀድሞ ስለሚሆነው ታላቅ የሃይማኖት ክህደት ሲናገር** ‹‹ ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና። ›› ***ካል ተሰ 2:3 ፡፡*** **ብሎናል፡፡**
- **ሐዋርያው** ‹‹ገና በጣም ጥቂት ጊዜ ነው፥ ሊመጣ ያለውም ይመጣል አይዘገይምም፤ ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል ወደ ኋላም ቢያፈገፍግ፥ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም። እኛ ግን ነፍሳቸውን ሊያድኑ ከሚያምኑቱ ነን እንጂ ወደ ጥፋት ከሚያፈገፍጉ አይደለንም። ›› ***ዕብ 10:37-39፡፡*** **በማለት ጽፎልናል፡፡ ሐዋርያው በዚህ ክፍል የተናገረው በእምነት ኖረው ስለካዱት ነው፡፡**
- አምነው የሚክዱት የተመረጡ አይደሉምና ይክዳሉ፤ ምክንያቱም የተመረጡት በሕይወታቸው ወይም በዘመናቸው ሁሉ ጌታቸውን እስኪገናኙት ድረስ በእምነታቸው በሃይማኖታቸው ይጸናሉና፡፡
- ከላይ የተገለጹት የማይበረታቱ የእምነት ዓይነቶች ናቸው፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪

## የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው

## የእምነት ደረጃዎች

### *9. የሚያድግ እምነት*

- **ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ምዕመናን** ‹‹ወ ንድሞች ሆይ፥ እምነታችሁ እጅግ ስለሚያድግ የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን፤ ›› ***ካል ተሰ 1፡3፡፡*** **እንዲሁም ለቆሮንቶስ ምዕመናን እምነታቸው ያድግ ዘንድ** ‹‹ ነገር ግን በነገር ሁሉ፥ በእምነትና በቃል በእውቀትም በትጋትም ሁሉ ለእኛም በፍቅራችሁ እንደ ተረፋችሁ፥ በዚህ ቸር ሥራ ደግሞ ትረፉ›› ***ካል ቆሮ 8፡7፡፡*** **በማለት ጽፎላቸዋል፡፡**
- **እምነት እንደ በጎ ሥራዎቻችን የሚያድግ የሚለመልምም ነው፡፡**

### *10. የምንጠብቀው እምነትን(ሃይማኖት)*

- **ሐዋርያው በመጨረሻ ቀናቶቹ** ‹‹መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።›› ***ካል ጢሞ 4፡7-8፡፡*** **በማለት ስለራሱ ተናግሯል፡፡**
- **ለቆላስይስ ምዕመናንም** ‹‹ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ፥ በሃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል። ያም ወንጌል ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ዘንድ የተሰበከ ነው ›› ***ቆላ 1፡23፡፡*** **ብሏል፡፡**

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

### *11. የምናጸናው እምነት*

- **ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ከሰይጣን ስለሚኖረው ፈተና ሲመክረን** ‹‹በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።›› ***<u>ቀዳ ጴጥ 5፡9፡፡</u>***

### *12.በእምነት ባለጠጋ  የሚያደርገን እምነት (ሃይማኖት)*

- **ሐዋርያው ያዕቆብ** ‹‹እግዚአብሔር በእምነት ባለ ጠጎች እንዲሆኑ ለሚወዱትም ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን?›› ***<u>ያዕ 2፡5 ፡፡</u>*** **እንደተናገረው ማለት ነው፡፡**

### *13. ሙሉ የሚያደርገን እምነት*

- **ስለ ሐዋርያው ቅዱስ እስጢፋኖስ** ‹‹ይህም ቃል ሕዝብን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ፊልጶስንም ጵሮኮሮስንም ኒቃሮናንም ጢሞናንም ጳርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ። በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው፥ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው።›› ***<u>የሐዋ 6፡5-8፡፡</u>***

- **የሚከተሉት ምልክቶችም ለእምነት (ለሃይማኖት) ሕይወት ቁልፍ ናቸው፡፡**

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

### *14.በፍቅር የሚሠራ እምነት*

- **ቅዱስ ጳውሎስ** ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና።›› ***<u>ገላ 5፡6፡፡</u>*** ‹‹**የሚሠራ እምነት**›› **ተብሎ የተጠቀሰው ያለሥራ እምነት የሞተ ስለሆነ ነው፡፡** ***<u>ያዕ 2፡20፡፡</u>*** ‹‹**ፍቅር**›› **ተብሎ የተጠቀሰው** ‹‹በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል።›› ***<u>ማቴ 22፡40፡፡</u>*** **የተባለው ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ ነው፡፡**

### *15. ተአምራትን የሚሠራ እምነት*

- **ጌታችን ስለዚህ ሲናገር**‹‹ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፡፡›› ***<u>የሐዋ 6፡5-8፡፡</u>*** **ብሎናላ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም** ‹‹የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል።›› ***<u>ያዕ 5፤15፡፡</u>*** **ብሎናል፡፡**
- **የዚህም ነገር ጫፉ (ፍጻሜው) ጌታችን** ‹‹ለሚያምን ሁሉ ይቻላል፡፡›› ***<u>ማር 9፡23፡፡</u>*** **በማለት የተናገረው ነው፡፡**

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፪</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎችና ዓይነታቸው</u>

## <u>የእምነት ደረጃዎች</u>

### *16.መጠራጠር የሌለበትና ፍጹም በእግዚአብሔር የማመን ሃይማኖት*

- ጌታችን ተአምራት የተደረገላቸውን የጠየቃቸው ጥያቄ የሚያመለክተን እንዲህ ያለውን እምነት ነው፡፡ ‹‹ታምናለህ?›› በማለት ይጠይቅ ነበርና፡፡ ይፈውሳቸው ዘንድ የጠየቁትን ዕውራን ‹‹ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን? ›› <u>***ማቴ 9፡28፡***</u> ብሎ ጠይቆአቸዋል፡፡
- ጌታችን ለከነናዊቱ ሴት ‹‹አንቺ ሴት፥ እምነትሽ ታላቅ ነው፡፡›› <u>***ማቴ 15፡28***</u> እንዲሁም መቶ አለቃውን ‹‹እውነት እላችኋለሁ፥ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም።›› <u>***ማቴ 8፡10***</u> በማለት እንደተናገረው እንዲህ ያለውን ጥርጥር የሌለበትን እምነት ባርኮታል፡፡

### *17. ፍጹም የሆነ እምነት*

- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ያተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ…፡›› <u>***ቀዳ ቆሮ 13፡2፡፡***</u> በማለት የተናገረው፤ ተራራን የሚያፈልስ እምነት የሚልቀው የሌለ የእምነት ሁሉ ጫፍ ፍጹም እምነት መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡ … የእምነት ዓይነቶች …ሐሳባዊ፣ ተግባራዊ…

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org